# ኢትዮጵያ አትፈርስም !!

***መስፍን ማሞ ተሰማ***

***ሀገሬ ውዴ ኢትዮጵያዬ ሆይ !***

እኔ ዛሬም ያው የጥንቱ ልጅሽ ነኝ። ተሰድጄም ቢብስ እንጂ ፍቅርሽ ከቶም አልበረደም። በዕድሜ ኸረት እንኳ አልሰከነም። ብትርቂኝም ልቤ አልራቀም። ስወለድ ኢትዮጵያዊ ስሞትም ኢትዮጵያዊ ነኝና ። አዎ ሀገሬ ፤ ድገምልኝ ካልሽኝ እደግመዋለሁና - ስወለድ ኢትዮጵያዊ ስሞትም ኢትዮጵያዊ !!

ይልቅስ ሀገሬ ጉድ ካልሰማሽ የተደገሰልሽን ጉድ ላሰማሽ። ኢትዮጵያ ሆይ ስሚ። እነሆ ዘንድሮ ላንቺ ብቻ የተዶለተ "ስምንተኛው ሺህ" ታውጆብሻል። በአህጉረ አውስትራሊያ - ከሜልበርን ፤ በምድረ አውሮፓ - ከለንደን። እነሆ ሊያፈርሱሽ ፤ እነሆ ከምድረ ገፅ ሊያጠፉሽ ዝተዋል ፤ በር ዘግተው ተማምለዋል ፤ ውል ቋጥረው አጨብጭበዋል።

ደግሞ ከወዲያ በአውደ ምድርሽ የሚርመሰመሱ ወያኔ ፋሽቶችና ባንዶች ብአዴን ወኦህዴድ ወደኢህዴግ - በናዚስት አጋዚ እየታገዙ - እነርሱም የራሳቸውን የምፅዐት ዘመን አዋጅ አስነግረውልሻል።

ውዴ ሆይ ፤ በውስጥም በውጪም ተወግተሻል። ወያኔ በቅኝነት ሊገዛሽ ፤ ሊረግጥሽ ፤ ሊመዘብርሽ - ካልቻለ ሊያጨራርስሽ። ፅንፈኛ ኦነጎች በጥላቻና በቂም በቀል ሊያጠፉሽ ሊበታትኑሽ። እንግዲህ እሳት ካየው ምን ለየው? ከውስጥ ኢህአዴግ ከውጪ ኦነግ ሰደድ እሳት ሊለቁብሽ ፤ በአደባባይ አውጀዋል ሊበታትኑ ሊያጠፉሽ። የፋሽስት ወያኔ ፅዳው ገብስ ነው ባንልም ፤ ከላያችን ማሽቀጠራችን ግን አይቀርም። እና ስለነርሱ አልነግርሽም ፤ ታውቂያለሽና አንቺም።

ይህም ሆኖ ግን ውዴ፤ *<u>በፅንፈኞቹ ኦነጎች ፅንፈኛ የለንደን አዋጅ ምክንያት ወያኔ ፋሽስትን እና ባንዳ አጋሮቹን ለማስወገድ መክፈል ከነበረብን በላይ ውድ ዋጋ እና የተራዘመ ጊዜ ሳያስከፍለን ግን አይቀርም።</u>* ይህ ብቻም አይሆንም። በኒህ የምፅዐት ዘመን አዋጅ ነጋሪና አጨብጫቢ ተሰብሳቢዎች ሳቢያ በባዶ እጃቸው ለነፃነት በሚፋለሙ የኦሮሞ ልጆቻችን፤ ወንድሞቻችን፤ እህቶቻችን፤ ዘመድ አዝማዶቻችን፤ ጎረቤቶቻችንና አብሮ አደግ ጓደኞቻችን ላይ ፋሽስት ወያኔ እና ባንዶች እያዘነቡት ያለው ዕልቂትና መከራ ሳያንስ እነሆ በዚህ የጭራቅ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት እኒህ ሃላፊነት የጎደላቸው ፅንፈኞች *እሳት የሚተፋ መትረየስ አቀብለውታል። በእነርሱ ምክንያት በኦሮሞ ወገኖቻችን ላይ ከእንግዲህ ለሚደርሰው ጥፋት ሁሉ ለንደን ላይ ያጨበጨቡና የዛቱ ተጠያቂዎች ናቸው።* መቼም ኦሮሞ ሁሉ ኦነግ አይደለም እንጂ ፤ የፅንፈኛ ኦነጎች መሪር ጥላቻና ዛቻ ግን ከወያኔ "እኔ ከሌለሁ ኢትዮጵያ የለችም" የግብዝነት አዋጅ በምን ሚዛን ነው እሚያንስ? እሳት ካየው ምን ለየው ? ሀገር መበታተን ማፈራረስ ፤ ህዝብ ለህዝብ ማጨራረስ - ኢህአዴግም አደረገው ኦነግ ግቡ ያው አንድ ነው ። ኢትዮጵያን ማፍረስ። ኢትዮጵያዊነትን መደምሰስ - ግና ከንቱ ቅዥት !!!

መከባበርን አክብረን ዝም ብንል፤ ኦነጋውያን ፅንፈኞችን ከአንደበታችን ተቆጥበን ብናባብል ፤ በለዘበ ቋንቋ ብናሽሞነሙን የወንድማማችነታችንን፤ የእህትማማችነታችንን እንጂ - የአብሮ አደግነታችንን እንጂ ፤ የነገን ብለን እንጂ፤ የልጆቻችንን ሠላም ብለን እንጂ ፤ የደም የታሪክ ቁርኝታችንን ብለን እንጂ - አልነበረም ኢትዮጵያዊነታችንን ማሻሻጣችን። ወይም ኦነግን መፍራታችን።

እነሆ በኢትዮጵያዊነትና በኢትዮጵያ ላይ በፅንፈኛ ኦነጋውያን የታወጀውን የምፅዐት ዘመን "የስምንተኛውን ሺህ" አዋጅ በየፈረጁ እያቀረብን እንሞግታለን።

<u>ከሜልበርን አውስትራሊያ፤ በ'ኤስቢኤስ' ሬዲዮ</u>

*'ኢትዮጵያዊ ማንነት የሚባል የለም። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ማንነት የሚባል ነገር የለም ፤ ከአማራና ከትግሬ ውጪ።" ፀጋዬ ረጋሳ አራርሳ (ዶ/ር) ለኤስቢኤስ ሬዲዮ ከሰጠው ሰፊ መግለጫ የተወሰደ። (የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ዶክተር ፀጋዬን አንተ ማለቱ በኢትዮጵያዊነት ባህሉና ወጉ የዕድሜን ዘለላ ማክበሩና ቦታ መስጠቱ እንጂ 'ማሳነሱ' አይደለም፤ ይህም ዶ/ሩን የሚጠፋው አይመስለኝም)።*

"ኢትዮጵያዊ ማንነት የለም' ሲባል "ኢትዮጵያዊ የሚባል የለም" ማለት ነው። እነሆ እኔም እላለሁ። ኢትዮጵያዊ ማንነት አለ። ምክንያቱም ኢትዮጵያዊ አለና። ምክንያቱም ኢትዮጵያ አለችና። ዶ/ሩ ኢትዮጵያዊ ማንነት ላለመኖሩ የሰጠውን ረዥም ዲስኩር ነጥብ በነጥብ በመሞገት ወርቃማ ጊዜዬን ላጠፋ አልሻም። ጉንንጭ አልፋ ነውና። ግን እኔም አለሁ። እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ። ኢትዮጵያዊ ያደረገኝም ኢትዮጵያዊ ማንነት ስላለኝ ነው። ኢትዮጵያዊ ሰብዕና ስላለኝ ነው። በቃ!!

ኢትዮጵያዊ ሰው *አክባሪ* ነው። የሰውን *መብትና* ማንነት *እመር* ብሎ አይደፍርም፤ አይተነኩስም። እንተ ዶ/ር ፀጋዬ እኔን አታውቀኝም። እኔም አላውቅህም። ወይም አልደረስኩብህም። **የኦሮሞ ማንነት የለም ብዬ ስናገር ሰምተኸኛል? ወይስ ፅፌ አንብበኸል?** "ኢትዮጵያ እንደማንነቴ ለኔ ቦታ ኖሯት አያውቅም አለክ" ይህን ማለት *መብትህ ነው።* ያቀረብካቸው ምክንያቶች ግን ከቶም ሀገራዊ ፋይዳ የያዙ ፤ ከግለሰባዊ ኩርፊያ የዘለሉና በትልቁ ማዕቀፍ (ቢግ ፒክቸር) ምልከታ ጠቢባዊ (ዊዝደም) የተላበሰ ራዕይ የታጀቡ አይደሉም። ይህም ሆኖ - እጀ መንገዴን ፃፍኩልህ እንጂ - የማኩረፍ *መብትህን አልተጋፋሁም። ማኩረፍ ትችላለህ።* አንተ ግን ሳታውቀኝ ፤ ሳልደርስብህ - *መብትህን ሳልጋፋ ፤ ማንነትህን ሳለጨፈልቅ -* ሜልበርን ላይ በሚገኘው ሬዲዮ በአለም ዳርቻዎች ሁሉ - ከአፅናንፍ አፅናፍ - **ኢትዮጵያዊ ማንነት ብሎ ነገር የለም ብለህ ኢትዮጵያዊ ማንነቴን በአየር ሞገድ ደመሰስከው።** ምን ተሰማህ ዶ/ር ፀጋዬ? ልብህ በደስታ ጮቤ ረካች? *<u>የኦሮሞነት መብቴ ይከበር እያልክ የሌሎችን መብት በአደባባይ ያለ አንዳች ማቅማማትና አዘኔታ ስትጨፈልቅ ለመሆኑ ለሰከንድ እንኳን የሰብዐዊ መብትን ህግ አስታውሰኸል?!</u> በሜልበርን ዩኒቨርሲቲ መምህርነትህ ስለ ሰብዐዊ መበት ማስተማር አይደለምን? ድንቅ ነው። 'ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ' አሉ አባቶች።*

እርግጥ ነው አንተ የፋሽስት ወያኔን 'ህገ *መንግሥት'* ትደግፋለህ ፤ የፋሽስት ወያኔን 'ፌዴራሊዝም' ህገ *መንግሥት* ታደንቃለህ ፤ አሰራሩን እንጂ። እኔ ደግሞ ኦነግና ወያኔ ያረቀቁትንና ያፀደቁትን (ዛሬም ኦነጋውያን እንደ ገድል የሚያወሩለትን) ህገ *መንግሥትም* ሆነ 'ፌዴራሊዝሙን' ጭምር እፋለማለሁ። የህግ መምህር መሆንህንም ሰምቻለሁ። ያልደረሰብህን ሰው *መበት* በአደባባይ ጥሰህ ህግ ስታፈርስ አየሁህ እንጂ።

ሀገር በቀሉ ቅኝ ገገር ህወሃትና አጋሮቹ አዲስ አበባን 'አዱ ገነት"ን ከመቆጣጠሩ ዋዜማ ጀምሮ ሀገሬን ለቅቄ ፤ ለፋሽስት ወያኔ አልገዛም ብየ የኖርኩ ሰው ነኝ። (በነገራችን ላይ 'አዱ ገነት' አዲስ አበባዬ እትብቴ የተቀበረባት የትውልድ እና የእድገት *መናኸሪያዬ* ክፉና ደጉን ያሳለፍኩባት ማህደሬ ናት። ያው እንደምታውቀው ግን ከደደቢት የመጣው ቅኝ ገገር ፋሽስት ወያኔ ሰፈሬን አፍርሶ ከሰፈሬ አባሮኛል፤ ወደፊት ደግሞ 'ኢትዮጵያን ማፍረስ ከቻለ" ፅንፈኛው አነግም በመሬት ባለቤትነት ጭርሱን 'ሰቴትለስ' ሳያደርገኝ ይቀራል ትላለህ?) እና ደግሞ የግንቦት ገብርዔል ለት ሀገሬን ለቀቅሁ ስልህ ያው 'ለመፈረጀ' እንዳትቸኩል - ወንጀል የሰራሁ ደርግም/ኢሰፓም አይደለሁም።

ደርግም/ኢሰፓም እንኳ ብሆን ከወያኔ አልብስምና ግዴለኝም። ግና ወያኔ ሀገሬን በዘር በክል መፈረጁን ፤ ኢትዮጵያዊነትን አዋርዶ በጎጥ በቀበሌ ማዋቀሩን በመፋለም ሀገሬን ለቀቅሁ እንጂ። ታዲያ - የነርሱ ሳያንሰኝ - አንተ ዶ/ር ፀጋዬ በስደት በምኖርበት ዓለም የሠላም እንቅልፍ እንኳ እንዳልተኛ **ወያኔ እንደሚፈርጀው ወያኔ ታርጋ እንደሚለጥፈው የፈረጅከኝ በምን ተዳዬ ነው?** የት ታወቀኛለህ? አማራ ልሁን ኦሮሞ፤ ጉራጌ ልሁን ከንባታ ፤ አገው ልሁን ወላይታ ፤ አፋር ልሁን ኮንሶ የሁለት ጎሳ ውሁድ ልሁን ወይም የሁሉ ጎሳ ድብልቅ - የት ታውቀኝና ነው **“ኢትዮጵያዊ አማራና ትግሬ ነው”** ብለህ አፍህን ሞልተህ በከፍተኛ ፌሽታ እንደ ወያኔ ፈርጀኸኝ የተናገርከው? ወያኔ ኤስቢኤስ ላይ መጥቶ እንዲህ ቢለኝ አይደንቀኝም ፤ ትግሬን ግን እሱ ከአማራ ጋር አይደባልቅም እንጂ። እንደው ሌላው ቢቀር አውስትራሊያ ውስጥ እየኖርክ እንዴት የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል መቻቻልን አላስቻለህም?

*ለመሆኑ በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ፤ አባቶቻችን ባቋቋሙት የአፍሪካ አንድነት ከአፅናፍ አፅናፍ የምትታወቅን ሀገርና ህዝብ “ኢትዮጵያዊ ማንነት ብሎ ነገር የለም”* ብለህ የአዋጅ ደበሎ ስትቀድና *የአንድን ህዝብ ማንነቱንና የሀገር መገለጫውን ስትገፍና ከመሬት ስታፈርጥ አንተ ዶ/ር ፀጋዬ የመጀመሪያው እንደሆንክ ታውቃለሁ?* ለዚህ ግብዐትህ በጊነስ ላይ በሬኮርድ ቀዳሚነት ብትመዘገብ የሚደንቅ አይሆንም።

ባንተ ቤት - ኢትዮጵያዊነት የአማራና የትግሬ ከሆነ እንግዲህ እኔም (በእናቴ ወይ በአባቴ ከትግራይ ወይ ከአማራ የሚቋጠር ሀረግ የለኝምና) ወይ ወደ ጎጤ ልሂድ ብዬ ወይ ያንተን ቡድን ወይ የዛኛውን እንድቀላቀል ፤ አልያም ቅስሜ እንዲሰበርና ኢትዮጵያዊ ሆኜ መፈጠሬን እንድረግም እንዳማርር አስበህና አልመህ ከሆነ ከሸፎብኻል። ለምን ብትል - ኢትዮጵያዊ ማንነት አለና። እኔ አለሁና። እኔም ኢትዮጵያዊ ነኝና። በሚሊዮናት ወሚሊዮናት የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ነን የሚሉ ኩሩ የኦሮሞ፤ የአማራ፤ የጉራጌ፤ የአፋር፤ የሐረር፤ የሲዳማ፤ የጋንቤላ ፤ የኮንሶ፤ የትግራይ…ነገድ/ጎሳ ተወላጆች በምድረ ኢትዮጵያ፤ በአፍሪካ ሀገራት፤ በአውሮፓ፤ በሀገረ አሜሪካ ፤ በአውስትራሊያ፤ በኒውዚላንድ ፤ በኤዢያና በመካከለኛው ምሥራቅ እናም በደቡብ አሜሪካ ይገኛሉና፤ አሉና። አለንና !!

ዶ/ር ሆይ ! መማር ለራስ ነው። ሰው የሚማረው ለእንጀራው ነው። ለቢዴና። ለኑሮው። ተምሮ በሚያገኘው ሙያዊ ዕውቀት (ፕሮፌሽናል ኖውሌጅ) ኑሮውን ይመራል። ህይወቱን ያሻሽላል። ሀኪም፤ መሃንዲስ፤ የህግ ጠበቃ፤ ዳኛ፤ አስተማሪ /ሌክቸረር/፤ ኢኮኖሚስት ፤ ሳይንቲስት ወዘተርፈዎች ሙያዊ ዕውቀት የሚያስገኛቸው ናቸው። እኒህ የሙያ ዘርፎች የእንጀራ መብያ የዕውቀት (ኖውሌጅ፤ስኪል) ውጤት ናቸው። በቃ። ሙያዊ ዕውቀት (ፕሮፌሽን) መልካም ሥራ ያስገኛል። በሃላፊነት ያስሾማል። ሙያዊ ዕውቀት (ፕሮፌሽናል ኖውሌጅ) መኖር ማለት ግን ጠቢብነትን ወይም ሊቅነትን (ዊዝደም) ተላብሷል ማለት አይደለም። የኢትዮጵያ ፖለቲከኛ “ምሁራን/ልሂቃን” በአብዛኛው ችግራቸው ይህ ነው።

*ኢትዮጵያን ወደ ገደል ጫፍ ፖለቲካ እየመሯት የሚገኙ በሙያዊ ዕውቀታቸው ዲግሪ ወይ ዲግሪዎች የጫኑ ዶክተሮች ፕሮፌሰሮች ወዘተርፈዎች ችግራቸው ዕውቀት (ኖውሌጅ) ሳይሆን ጥበብ (ዊዝደም) ነው። የኢትዮጵያን ፖለቲካ የሚመሩ “ምሁራን/ልሂቃን” ዕውቀት ብቻ ሳይሆን ጥበብ (ዊዝደም) እስከሌላቸው ድረስ የሀገራችንና የህዝባችን ሰቆቃ ይቀጥላል።* ለዚህ ግዙፍ ማስረጃው የለንደኑን ኮንፍረንስ ተናጋሪዎችና አይዟችሁ ባዮችን አዳራሽ የሞሉ አጨብጫቢዎች መመልከት ነው። ለዚህ ግዙፍ ማስረጃው እጅግ ከፍተኛ የሆነ የዊዝደም ድህነት “ዲፌሲት’ ያለበትን የፅንፈኛውን ኦነግ የጃዋር መሀመድን ፓለቲካዊ ጉዞ እስከ ለንደን መመልከት ነው። ይህ ሀሰት ነው ካልክ - ዶ/ር ፀጋዬ - የራስህን አዋጅና ድርጅትህን(?) ትፈትሽበት ዘንድ እጋብዝኻለሁ።

*“Knowledge is nothing more than an accumulated raw of facts, but wisdom is the ability to see people, events and situations as God see them” (www.gotquestions.org)*

*“ዕውቀት የጥሬ ዕውነቶች ክምችት ነው፤ ጥበብ ግን የሰው ልጅን (ህዝብን)፤ ክስተቶችንና ተግዳሮቶችን እንደ እግዚአብሄር ለመመልከት የሚያስችል ነው።” (ትርጉም የፀሀፊው)*

ዶ/ር ሆይ፤ የህግጋት ሁሉ መሰረት፤ የህግጋት ሁሉ ሀሌታ የህግጋት ሁሉ አለት ***“በራስህ ላይ ሊያደርጉብህ የማትፈልገውን በሌሎች ላይ አታድርግ”*** ይላል። ይህ የህግጋት ሁሉ ዐልፋና ዖሜጋ ነው። ምድራዊ ህግጋት ሁሉ የመነጩት ከዚህ ዘለዓለማዊ ክቡር ህግ ነው። ይህንን ህግ ስትተላለፍ ትቀጣለህ። ይህንን ህግ ስትተላለፍ ሀጢያት ትሰራለህ፤ ሀጢያትም ወንጀል ነው። (ምድራዊው ህግ አድኋዊነቱ ግድፈቱና ጨቋኝነቱ አሊያም ዴሞክራሲያዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) ህገ መንግሥት ብትል ወንጀለኛ መቅጫ፤ የሽብርተኛ ህግ ብትል የሚዲያ . . . ከዚህ አንድና አንድ የህግጋት ሁሉ ዛፍ የወጡ ቅርንጫፎች ናቸው። አንተ ዶ/ር ፀጋዬ - የህግ መምህሩ - በኤስቢኤስ ላይ ቀርበህ **የገረሰስከው ህግ ይህንን የህግጋት ዛፍ ነው። ኦሮሞነትህን ለማስረፅ ኢትዮጵያዊነቴን በዓለም አደባባይ መግሰስህ !! መግሰስህ ሳያንስህ ደግሞ መፈረጅህ !!**

ነገር ግን እልኻለሁ - *በዚህ ሃላፊነት በጎደለውና በጭካኔና በቀል በታጀለውን ህገ ወጥ አዋጅህ እጅግ በጣም ጎድተኸኛል። ሳልደርስብህ ደርሰህብኛል። እጅግ በጣም አሳምመኸኛል። ሳልነካህ ገፍትረኸኛል። እጅግ በጣም አሳዝነኸኛል። ሳልበድልህ በድለኸኛል። ሳላሳምምህ አቁስለኸኛል። ከሁልም በላይ ግን - ሠላምህን ሳልነካብህ ፤ ሠላሜን ነጥቀኸኛል፤ ሠላሜን ገፈኸኛል። እግዜር የሥራህን ይስጥህ !!*

## <u>ከምድረ አውሮፓ - ለንደን (በኦሮሞ ህግ አውጪዎች የተጠራ የኦሮሞዎች ኮንፍረንስ)</u>

ለፋሽስት ሀገር በቀል ቅኝ ገዢ ወያኔ አገር አቋራጭ ተምዘግዛጊ ሚሳይል ሆን ብሎ የሰጠ ወይም ያቀበለ ኮንፍረንስ። በዚህ ኮንፍረንስ በኢትዮጵያ ላይ የወረደባት የጥላቻ የቂም በቀልና የጥፋት ዛቻ እጅግ የሚያስደነግጥና የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን በአዳራሹ የታደሙ ሁሉ እጃቸው እስኪቃጠል ለኢትዮጵያ መበተን ሲያጨበጭቡ የዋሉ የክፉ ሰዎች መንፈስ ጣራ ነክቶ የተመለከትንበት ነው። እንዲህ ያለ የጥላቻና የቂም በቀል መንፈስ የሰፈነበት ጉባዔ በዕድሜ ዘመኔ አይቼ አላውቅም። ወደፊትም እማይ አይመስለኝም። (አምላክ በዚህ በቃችሁ ይበለን!)።

በዚያ የጥፋት መድረክ ላይ እንዲህ ሲሉና ሲያጨበጭቡ ዋሉ ፤ *በአጭሩ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት የሚል ነገር የለም። ኢትዮጵያን መበታተን ነው ዓላማችን። ኢትዮጵያ ስትበታተን ብቻ ነው ኦሮሞ ሠላሙን የሚያገኘው። ኦሮሞ በንቃት ተደራጅቶ ፤ ታጥቆ ኢትዮጵያን መበታተን አለበት። ኢትዮጵያ ከተበታተነች በሁዋላ ሌሎች ከፈለጉ ከኦሮሞ ጋር መሆን ይችላሉ። (የመጨረሻውን አባባል ፅንፈኛው ኦነግ ጃዋር መሀመድ ተናገረው፤ ሌሎቹን ግን ሌሎች ፅንፈኛ ኦነጎች)*

እግዚአብሄር ይሁነን እንጂ፤ የጥፋት ዘመን ጀማሪዎች ስብስብ ምን ይመስላል ከተባለ የለንደኑን ኮንፍረንስና ደም ሥራቸው በጥላቻ እየተገታተረ አየሩንና ጠረጴዛውን በቡጢ ስደበድቡ የዋሉትን ተሰብሳቢዎች መመልከት ይበቃል። እንደነዚህ ሰዎች የዛቻ የጥላቻና ቂም በቀለኝነት  መጠን ከሆነ አቧራው መጤሱና መተላለቃችን ነው። እግዜር ይሰውረን። አላህ ይታደገን።

እልቂትን፤ ውድመትን፤ ጥፋትን፤ በዚያች ምድር ላይ ምፅዐትን ለሚሹልን ሁሉ እኛም ሀገራችንን ኢትዮጵያንና ማንነታችንን ኢትዮጵያዊነትን ለመታደግ

በእግዚአብሄር አብ ሃይል ፤ በአላህም ችሮታ ፤ በፆም በፀሎት፤ በቤተ ክርስቲያናት ይሁን በመስጊዶች እየተገኘን በዚያች የፍጅት መጀመሪያ ጥይታቸውን በሚተኩሱበት ሰዓት የኢትዮጵያ አምላክ ሀይልንና ብርታትን እንዲሰጠን መማፀን ያለብን ወቅት ዛሬ ነው።

በእሳት ተከበናል። ኢትዮጵያ በእሳት ተከባለች። ኢትዮጵያውያን በእሳት ተከበናል። በሁለት ጥይት መሞታችን - ከወዲያ በፋሽስት ወያኔና ባንዶቹ፤ ከወዲህ በፅንፈኛ ኦነጋውያን - ካልቀረልን . . . መቼስ ምን እንላለን? ላይችል አይሰጥ ብለን ያው እንደ አብናቶቻችን (አባት እናቶቻችን) ባንዲራችንን ለብሰን (በወያኔና በፅንፈኛ ኦነግ ጥይት) እንወድቃለን። ሀይል የእግዚአብሄር ነውና !! ሀይል የአላህ ነውና !! እንኳን ከዛቱብን ከወረወሩብንም ያድነናልና። አዎ የዕምነት ሰዎች ነንና ይህንን እናምናለን። አዎ እኛ በፈጣሪ እናምናለንና ፤ እኛ በአላህ እናምናለንና - “ጥለን እንወድቃለን’ ብለን አንዝትም!! አንፎክርም!! ይልቁንም የአባታችንን (ይህ ፀሀፊ ኦርቶዶክስ በመሆኑ ነው ‘አባታችን’ ማለቱ) የፓስተር ዶ/ር ቶሎሳ ጉዲናን መልዕክት እንደግማለንና እነሆ ጎጠኞች ሁሉ ሆይ እነሆ ፅንፈኞቹ ኦነጎች ሆይ ከተቻላችሁ ስሙ!!! ልቡናችሁ ካመረረ ጥላቻና ቂም በቀለኝነት እንዲመለስም ከቻላችሁ ፀልዩ !!!

*… ወገኖቼ እግዚአብሄር ይድረስልን በሉ። ለምህረትና ለምሪት ወደ እግዚአብሄር መመለስ የማስተዋል እንጂ የድካም ምልክቶች አይደሉም። ባልጠበቅነው መንገድ የምድሪቱ ፅዋ እየሞላ ስለሆነ…ለርዳታ ወደ እግዚአብሄር መጮህ ምርጫ የለውም። እግዚአብሄር ይድረስልን በሉ። ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የምድሪቷ ብሄር ብሄረሰቦች በድብብቆሽ ዲፕሎማሲ ሳይሆን በልብ ግልፅነት ፊት ለፊት ተገናኝተው በመደማመጥና በመቀራረብ በንስሃና በይቅርታ በመቀባበል በማያዳግም ሁኔታ ያለፈውን በመቅበር ለወደፊት በምህረትና በፅድቅ ላይ የተመሰረተ በምድሪቷ ስፋት ከዳር እስከ ዳር የሠላም እጅ መዘርጋት ነው። ይህንን እጅ እግዚአብሄር የሰጠን ለሠላም እንጂ እንድንዋጋበት አይደለም። ይሄ ነው የሚያስፈልገው። መጠላላት፤ መበጣበጥ በዚህ ዘመን ለማንም አይጠቅምም።*

*ራዕያችን ፤ አጀንዳችን አንድነታችን ነው። ይልቁንስ ምድሪቷን ወደ አዲስ ምዕራፍ ለማስገባትና የተፈወሰ ህዝብ እንዲኖርባት ማድረግ በምህረትና በይቅርታ መንፈስ መኀዝ ግድ ነው። ያለው ትውልድ ውስጡ ተበላሽቷል። ጤናማ አስተሳሰብ ያለው የለም። አዲስ ትውልድን እግዚአብሄር ይስጠን። ይህ ጥላቻና ዘረኝነት ያሰከረው ትውልድ ከብሄር ብሄሩ ጋር ሙቤ ካልረገጠ የዓለም መጨረሻ ይመስለዋል። ሁሉ ነገር ራሱ። ሁሉ ነገር ክልሉ። ይሄ ዕብደት ነው። በዛ ልንቀጥል አንችልም።*

*ወገኖቼ በእኛ መጋጨትና መለያየት የሚጠቀሙ ለራሳቸው ብዙ ነገር የፈረሰባቸው የኛን ህልውና የሚጠሉ ሰዎች ብቻ ናቸው። በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ግሎባላይዜሽን ዓለምን አንድ ስንዝር ባደረገበት ወቅት ሰዎች ልዩነታቸውን አስወግደው ከኢኮኖሚ ዕድገት ድርሻቸውን ለመካፈልና ለልጆቻቸው የሥራ ዕድል ለመፍጠር ረዣዥም ድልድዮች እየሰሩ ነው። እኛ እዛው ልንጨራረስ ነው። … ይሄ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ነው። እዛቸው ክልል ፈጥረን በክልል የምንገዳደልበት ምክንያት ምንድን ነው? … እኛ አሁንም አማራ ትግሬ ኦሮሞ ከንባታ ሀዲያ ሲዳማ ጉራጌ ወላይታ ይሄን ያን እያልን ከድንጋይ ዘመን ትዝታ አልወጣንም። ትዝታችን ይሄ ነው። ለልጆቻችን እና ለትውልዳችን የምናተርፈው ያን ያህል ነው።*

*እግዚአብሄር የሰየመን መፅሀፍ ቅዱስ የሚጠራን የዓለም ህዝብ የሚያውቀን ኢትዮጵያ ብሎ ነው። ከዛ ውጪ ሌላ ስም እኔ አላውቅም። እግዚአብሄር የሚያውቀው ምድሪቱን እንደ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ ብሎ ነው የሚጠራት። እኛ ሌላ የምናውቀው ነገር የለም። የምንሰራውም የምናስበውም የምናገለግለውም የምንኖረውም ለዚህች እግዚአብሄር ኢትዮጵያ ብሎ ለሚጠራት ምድር ነው። አለቀ። ውጡ ካላችሁበት። ውጡ ከነዚህ ጥቃቅን ጣዖቶቻችሁ። … የኢትዮጵያ ህዝብ ትውልዱን*

*የሚያተርፍ ፣ ምድራቱን የሚታደግ ፀሎት መፀለይና ንሰሀ መግባት እንዲችል የዘለዓለም ዘለዓለም እግዚአብሄር ማስተዋልን ይስጠን።*

አሜን ይስጠን! ብለናል አባታችን ፓስተር ቶሎሳ ጉዲና። እግዚአብሄር ይባርክልን። ቸሩ መድሃኔዓለም እድሜና ጤናዎን ያብዛልን። እርሶን የመሳሰሉ መካሪ አባቶችን ይጨምርልን። የመካሪ ድሃ አያድርገን። አዎ! ፓስተር ቶሎሳ አብዝተው ይፀልዩልን:: ሀገራችን እንዳንጋሬ ተወጥራለች። ኢትዮጵያ በዙሪያዋ እሳት ተለኩሶባታል። ኢትዮጵያውያን በእሳት ተከበናል። ኢትዮጵያ አድኑኝ ትላለች። እነሆም ወደ ፈጣሪ እጆቿን ዘርግታለች፤ እና ዶ/ር ቶሎሳ ሆይ ፀሎትዎን አበርቱልን !!!

<u>ማሳረጊያ</u>

እነሆ የመጨረሻው ኢትዮጵያዊ በፅንፈኛ ኦነጋውያንም ሆነ በፋሽስት ወያኔ ወባንዳ ጥይት እስካልወደቀ ድረሰ ኢትዮጵያ አትፈርስም፤ ኢትዮጵያዊነትም አይሞትም!!

እነሆ የመጨረሻዋ ኢትዮጵያዊት በፅንፈኛ ኦነጋውያንም ሆነ በፋሽስት ወያኔ ወባንዳ ጥይት እስካልወደቀች ድረስ ኢትዮጵያ አትፈርስም፤ ኢትዮጵያዊነት አይሞትም!!

የኢትዮጵያ ትንሳዔ በትንታግ ወጣት ልጆቿ ዕውን ይሆናል!

አዲስቷ ኢትዮጵያ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ልጆቿ ትገነባለች !!

ኢትዮጵያ ትቅደም!

Ethiopia First!

ተፃፈ ጥቅምት 2009 ዓ/ም (ኦክቶበር መጨረሻ 2016)

ሲድኒ አውስትራሊያ፤ mmtessema@gmail.com

**************************************************************************

<u>መረጃዎች፤</u>

* በሚልበርን ዶ/ር ፀጋዬ ረጋሳ አራርሳ ከኤስቢኤስ ሬዲዮ ጋር ያደረገው ቃለምልልስ

http://www.sbs.com.au/yourlanguage/amharic/en/content/movement-freedom-charter-or-charter-unity-pt-2

* በለንደን በተካሄደው ኮንፍረንስ የኢትጵያን መበታተን አስፈላጊነት ያወጀው ቪደዮ፤

https://www.youtube.com/watch?v=KnG6mhUZCC0

* የዶ/ር ፓስተር ቶሎሳ ጉዲና ታላቅ መልዕክት

https://www.youtube.com/watch?v=W5vc1MIf__w